ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር

መመስረቻ ጽሁፍ

ስማችን፣ ዜግነታችን እና አድራሻችን ከዚህ በታች የሰፈረው እኛ የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኋላ «ማህበር» ተብሎ በሚጠራው) መስራቾች እና ባለአክሲዮኖች በ1952 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ (ከዚህ በኋላ «የንግድ ሕግ» ተብሎ በሚጠራው)፣ በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እንዲሁም አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ እና ከዚሁ ጋር በተያያዘው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አነስተኛ የፋይናንስ ስራዎችን የሚያከናውን አክሲዮን ማህበር ለመመስረት ውሳኔ ላይ የደረስን ሲሆን በዚህም መሰረት በእኛ በባለአክሲዮኖች የተፈረመ ካፒታል እና የተፈረሙ አክሲዮኖች፣የተከፈሉ እና ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት ከዚህ በታች በአንቀጽ 5 (አምስት) ላይ በስማችን ትይዩ በሚገኘው መሰረት ይህንን ማህበር አቋቁመናል።

አንቀጽ 1

የባለአክሲዮኖች ስም፣ ዜግነት እና አድራሻ

ተ.ቁ	የባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም	ዜግነት	የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የተከፈለ የአክሲዮን ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	አድራሻ				
						ከተማ	ክ/ከተማ	ቀበሌ (ወረዳ)	የቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር
1	አቶ ክፍሌ ብርሃኑ ወንድሙ	ኢትዮጵያዊ	2,000	2,000		አ.አ	ቦሌ	03	23/1065	0911206600
2	አቶ ደጀኔ ወ/ማርያም በንቲ	ኢትዮጵያዊ	3,000	2,900	100	አ.አ	የካ	13	አዲስ	0911203019
3	ወ/ሮ አለምፀሐይ አለሙ ባቦ	ኢትዮጵያዊት	300	300		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	02	አዲስ	0911248157
4	አቶ ፍቅሬ ዘውዴ ደጋጋ	ኢትዮጵያዊ	700	400	300	አ.አ	የካ	13	B553-18	0912506853
5	አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ ታደሰ	ኢትዮጵያዊ	300	150	150	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	01	አዲስ	0911209085
6	ወ/ሮ ወርቅነሽ መኮንን ጎንጥ	ኢትዮጵያት	300	300		አ.አ	የካ	02	MH39	0921778572
7	ወ/ሮ ዶኔክ ተስፋዬ ዘሞ	ኢትዮጵያዊት	250	250		አ.አ	የካ	08	870	0911214654
8	ወ/ሮ ሙሉ ጎበና ተሊላ	ኢትዮጵያዊት	100	100		አ.አ	ቦሌ	12	New	0921627774
9	አቶ ማይክል መንገሻ ደለሉ	ኢትዮጵያዊ	200	100	100	አ.አ	አራዳ	01	395	0911516040
10	አቶ አፈወርቅ ዮሐንስ ገርማሞ	ኢትዮጵያዊ	250	100	150	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	01	አዲስ	0911242303
11	ወ/ሮ ራሔል አካለወልድ ገ/ስላሴ	ኢትዮጵያዊ	300	200	100	አ.አ	አራዳ	11/12-03	1163	0911683737
12	አቶ ወሰን አስፋው ቅጤሳ	ኢትዮጵያዊ	500	500		አ.አ	ኮ/ተራንዮ	08	1904	0911206186
13	አቶ ቴዎድሮስ አብርሃም ሀብተሚካኤል	ኢትዮጵያዊ	1,000	500	500	አ.አ	ቦሌ	02	062	0911200325
14	አቶ ጋረደው አሰፋ ማሞ	ኢትዮጵያዊ	150	100	50	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	12	1208	0911665920
15	አምባዬ አጋቶ አናታ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ቦሌ	6	155	0924849898
16	የኔነሕ ሙሉጌታ ደነቀ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	12	አዲስ	0911542854
17	አቶ ጌታቸው ማሞ አረዳ	ኢትዮጵያዊ	200	100	100	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	1	አዲስ	0911642573
18	አቶ ያሰቦብ ኢማያስ ኪዳኔ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	አራዳ	7	498/ለ	0911903061
19	አቶ ገበየሁ አበራ አየለ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	4	1507	0925273468
20	አቶ ጌታሁን ካሣዬ መኩሪያ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ቂርቆስ	8	24/	0913853776
21	አቶ ምስጋና መኩሪያ ዱራ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	4	438	0911424992

	ተባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም	ዜግነት	የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የተከፈለ የአክሲዮን ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	አድራሻ				
						ከተማ	ክ/ከተማ	ቀበሌ (ወረዳ)	የቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር
22	አቶ አብዲ በቶለ ሀይሉ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ጉለሌ	07	962	0923992346 0911448996
23	አቶ ይገረም ካሣ አባከህ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ቦሌ	11	B11/30	0911677459
24	አቶ አስናቀ አማኑኤል አያሌ	ኢትዮጵያዊ	250	250		አ.አ	ቦሌ	03	19/271	0943044503
25	ሰማ ደገፋ ጉደታ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	300	200	100	አ.አ	ቦሌ	03	2032	0912625778
26	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ	ኢትዮጵያዊ	1,000	1,000		አ.አ	ቦሌ	03	2185	
27	ወ/ሮ ትዝታ ከተማ ወዴሳ	ኢትዮጵያዊት	100	100		አ.አ	ቦሌ	01	አዲስ	0911632399

አንቀጽ 2
የማህበሩ ስም

የማህበሩ ስም «ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር» ተብሎ ይጠራል።

አንቀጽ 3
የማህበሩ አድራሻ

1) የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር ዋና መ/ቤት አድራሻ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን ስራውን የሚያከናውንበት የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፤አ/አበባ፤ ቦሌ ክ/ከተማ፤ ቀበሌ 03/05፤ የቤት ቁጥር አዲስ፤ ቤላ ሕንጻ፤ 1ኛ ፎቅ፡ የቢሮ ቁጥር 109 ይሆናል።

2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊከፈቱ ይችላሉ።

አንቀጽ 4
የማህበሩ የስራ ዓላማ

ማህበሩ የተቋቋመው የሚከተሉትን የንግድ ተግባራት ለማከናወን ነው።

1) ከገንዘብ አስቀማጮች ገንዘብ መሰብሰብና በገጠርና በከተማ በግብርና፤በጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች እንዲሁም በሌሎች መሰል ስራዎች ለተሰማሩ ሰዎች ጣራው በብሄራዊ ባንክ በሚወሰን የብድር መጠን እና የወለድ ታሪፍ መሰረት የብድር አገልግሎት መስጠት፤

2) ሌሎች በአዋጅ ቁጥር 626/2001 የተደነገጉ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አክሲዮን ማህበሩ ከዚህ የሚከተሉትን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊያከናውን ይችላል። እነዚህም

ሀ. የውጪታም ሆነ የግጪታ ቁጠባ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፤

ለ. በገጠርና በከተማ በግብርና እና በሌሎችም ስራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች ብድር መስጠት፤

ሐ. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፈሉ የሃዋላ ክፍያዎችን ማውጣትና መቀበል፤

መ. ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት አነስተኛ የመድህን ስራ መስራት፣

ሠ. ዓላማቸው ገቢ ማስገኘት የሆኑ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶች እና ሌሎች የአጭር ጊዜ የንግድ ወረቀቶችን ብሄራዊ ባንክ በሚወስነው መሰረት መግዛት፣

ረ. ስራውን የሚያከናውንባቸውን ህንጻዎች ጨምሮ ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት መያዝ መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፣

ሰ. በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች የተሰማሩ ደንበኞች የሚያካሂዱአቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶች ማገዝ፣

ሸ. ለደንበኞች የአመራር፣የገበያ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ምክር መስጠትና በእነዚህም መስኮች አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲችሉ ማገዝ፣

ቀ. ለጥቃቅንና ለአነስተኛ የንግድ ስራዎች ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፣

በ. በፋይናንስ ኪራይ አገልግሎት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 807/2013 መሰረት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ ለተሰማሩ ደንበኛ አርሶ አደሮች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና በአነስተኛ የስራ መስኮች የተሰማሩ ደንበኞችን ማገዝ፣

ተ. ብሄራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች በሚወሰኑ ሌሎች ስራዎች መሰማራት።

አንቀጽ 5
የማህበሩ ካፒታል እና አክሲዮኖች ብዛት

1) በማህበሩ የተፈረመ የአክሲዮን ካፒታል ብር 12,000,000.00 (ብር አስራ ሁለት ሚሊዮን) ነው።

2) ከላይ የተጠቀሰው የተፈረመ የአክሲዮን ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 1000 (ብር አንድ ሺ) ዋጋ ባላቸው 12,000 (አስራ ሁለት ሺ) ተራ የተመዘገቡ አክሲዮኖች ተከፋፍሏል።

3) ከተፈረመው የአክሲዮን ካፒታል ውስጥ ብር 10,350,000.00 (ብር አስር ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ) በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተፈጸመበት ሲሆን በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 312 መሰረት በማህበሩ ስም በሕብረት ባንክ አ.ማ ሚሊኒየም ቅርንጫፍ በዝግ የባንክ ሂሳብ አካውንት ውስጥ ተቀማጭ ተደርጓል።

4) ማህበሩ ከተመዘገበበት ዕለት አንስቶ በ6 (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ክፍያ ያልተፈጸመበት ካፒታል ሙሉ በሙሉ መከፈል አለበት።

5) በቡድን የተሰበሰቡ ግለሰቦች የገንዘብ መዋጮ በማድረግ በጋራ አክሲዮኖችን ሊገዙ ይችላሉ። በእንዲህ አይነት ጊዜ ባለአክሲዮኖቹ አንድ ተወካይ በመሰየም እንደ እነርሱ በመሆን በስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፍ በቋሚነት ተወካይ መሾም አለባቸው፣ወይም በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ሌላ ተወካይ ለመሰየም ይችላሉ።

6) በማህበሩ ውስጥ የአክሲዮን ይዞታ እንዲኖራቸው የሚፈቀደው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ላላቸው ሰዎች ወይም ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊያን ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅቶች ብቻ ይሆናል።

7) የማህበሩ አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ናቸው።

8) ሁሉም አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ይኖራቸዋል።

9) በንግድ ሕግ አንቀጽ 464 መሰረት የማህበሩን ካፒታል ማሳደግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አዲስ አክሲዮኖች ለሽያጭ በማቅረብ ወይም ባሉት አክሲዮኖች ዋጋ ላይ ጭማሪ በማድረግ የካፒታል ጭማሪ ሊደረግ ይችላል።

10) አዲስ አክሲዮኖች ለሽያጭ ከመቅረባቸው በፊት በንግድ ሕግ አንቀጽ 467 መሰረት የማህበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ መከፈል ይኖርበታል።

የማህበሩ ካፒታል እና የአክሲዮኖች ክፍፍል፤ በመስራች ባለአክሲዮኖች መካከል የተከፋፈሉ አክሲዮኖች ብዛት ከዚህ እንደሚከተለው ተመላክቷል።

ተ.ቁ.	የባለአክሲዮኖች ስም	የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የአንዱ የአክሲዮን ዋጋ (በብር)	ጠቅላላ የተፈረሙ አክሲዮኖች ዋጋ (በብር)	የተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት
1	አቶ ክፍሌ ብርሃኑ ወንድሙ	2,000	1000	2,000,000	2,000	
2	አቶ ደጀኔ ወ/ማርያም በንቲ	3,000	1000	3,000,000	2,900	100
3	ወ/ሮ አለምፀሐይ አለሙ ባቦ	300	1000	300,000	300	
4	አቶ ፍቅሬ ዘውዴ ደጋጋ	700	1000	700,000	400	300
5	አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ ታደሰ	300	1000	300,000	150	150
6	ወ/ሮ ወርቅነሽ መኮንን ጎንጥ	300	1000	300,000	300	
7	ወ/ሮ ዶኔክ ተስፋዬ ዘሞ	250	1000	250,000	250	
8	ወ/ሮ ሙሉ ጎበና ተሊላ	100	1000	100,000	100	
9	አቶ ማይክል መንገሻ ደለሉ	200	1000	200,000	100	100
10	አቶ አፈወርቅ ዮሐንስ ገርማሞ	250	1000	250,000	100	150
11	ወ/ሮ ራሔል አካለወልድ ገ/ስላሴ	300	1000	300,000	200	100
12	አቶ ወሰን አስፋው ቅጤሳ	500	1000	500,000	500	
13	አቶ ቴዎድሮስ አብርሃም ሀብተሚካኤል	1,000	1000	1,000,000	500	500
14	አቶ ጋረደው አሰፋ ማሞ	150	1000	150,000	100	50
15	አምባዬ ኦጋቶ አናታ (ዶ/ር)	100	1000	100,000	100	
16	የኔነሕ መሉጌታ ደነቀ (ዶ/ር)	100	1000	100,000	100	
17	አቶ ጌታቸው ማሞ አረዳ	200	1000	200,000	100	100
18	አቶ ያዕቆብ ኢሣያስ ኪዳኔ	100	1000	100,000	100	
19	አቶ ገበየሁ አበራ አየለ	100	1000	100,000	100	
20	አቶ ጌታሁን ካሣዬ መኩሪያ	100	1000	100,000	100	
21	አቶ ምስጋና መኩሪያ ዱራ	100	1000	100,000	100	
22	አቶ አብዲ በቀለ ሀይሉ	100	1000	100,000	100	

ተ.ቁ.	የባለአክሲዮኖች ስም	የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የአንዱ የአክሲዮን ዋጋ (በብር)	ጠቅላላ የተፈረሙ አክሲዮኖች ዋጋ (በብር)	የተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት
23	አቶ ይገረም ካሣ አባክህ	100	1000	100,000	100	
24	አቶ አስናቀ አማኑኤል አያሌ	250	1000	250,000	250	
25	ለማ ደገፋ ጉደታ (ዶ/ር)	300	1000	300,000	200	100
26	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ	1,000	1000	1,000,000	1,000	
27	ወ/ሮ ትዝታ ከተማ ወዬላ	100	1000	100,000	100	
	ጠቅላላ ድምር	12,000		12,000,000	10,350	1,650

አንቀጽ 6
የትርፍ ክፍፍል

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 452 እስከ 459 ላይ በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሰረት የትርፍ ክፍፍል ሀሳብ በዳይሬክተሮች ቦርድ መቅረብ አለበት፤በአንድ ጊዜ ክፍያ ከተገኘው ትርፍ ላይ ታክሶች፣ሕጋዊ ተቀማጭ፣ ሌሎች ተቀማጮች፣ አቅርቦቶች፣ የቀድሞ ኪሳራዎች እንዲሁም በውጭ ኦዲተሮች ምርመራ ከተደረገ በኋላ የሚጸድቁ ሌሎች ተቀናሾች ከተፈጸሙ እና በመጨረሻ በጠቅላላ ጉባኤው ከፀደቀ በኋላ መፈጸም አለበት።

አንቀጽ 7
የባለአክሲዮኖች ተጠያቂነት

ባለአክሲዮኖች የሚኖርባቸው ተጠያቂነት በማህበሩ ውስጥ በያዙት የአክሲዮን ብዛት ብቻ ይሆናል።

አንቀጽ 8
የማህበሩ አስተዳደር አካላት

ማህበሩ ከዚህ የሚከተሉት የአስተዳደር አካላት ይኖሩታል፦

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ
2. ኦዲተሮች
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ
4. ዋና ስራ አስፈጻሚ

አንቀጽ 9
የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣን

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም አዋጅ ቁጥር 626/2001 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የአክሲዮን ማህበሩ የበላይ አካል ሲሆን በንግድ ህጉ እና በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተካተቱት ስልጣኖች ይኖሩታል።

አንቀጽ 10
የዳይሬክተሮች ቦርድ

1) ማህበሩ ለ3 (ሶስት) ዓመታት የሚያገለግሉ እና በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ 9 (ዘጠኝ) አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይኖሩታል።

2) ዳይሬክተሮች በአንድነት የማህበሩ ተወካዮች ይሆናሉ።

3) በዚህ መሰረት የአክሲዮን ፈራሚዎች ጉባኤ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን 9 (ዘጠኝ) ባለ አክሲዮኖች የመጀመሪያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አድርጎ ሾሟቸዋል፦

1	አቶ አፈወርቅ ዮሐንስ ገርማሞ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ
2	አቶ ደጀኔ ወ/ማሪያም በንቲ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
3	አቶ ፍቅሬ ዘውዴ ደጋጋ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
4	አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ ታደሰ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
5	ወ/ሮ ዶኔክ ተስፋዬ ዘሞ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
6	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
7	ዶ/ር ለማ ደገፋ ጉደታ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
8	አቶ ይገረም ካሣ እባክህ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል
9	አቶ ጋረደው አሰፋ ማሞ	የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል

አንቀጽ 11
የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣኖች

የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖረዋል፦

1) የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ፣ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ፣

2) በተለይም የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣኖች አሉት፦

ሀ. የማህበሩን የአስተዳደር ስራ መቆጣጠር እና መከታተል፣

ለ. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሰልፈው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩን ስራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ፣

ሐ. በዋና ስራ አስፈጻሚ የሚቀርብለትን የማህበሩን መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የአስተዳደር ፖሊሲ እና ማንዋሎችን ማጽደቅ፣

መ. የማህበሩን ዋና ስራ አስፈጻሚ መሾም እና/ ወይም ማሰናበት፣

ሠ. የማህበሩን አመታዊ በጀት እና ዓመታዊ የስራ እቅድ ማጽደቅ፣

ረ. የማህበሩን ካፒታል መጨመርን ወይም መቀነስን በተመለከተ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ እና ሲፀድቅ ተግባራዊ ማድረግ፣

ሰ. በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች መሰረት ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበትን ሁኔታ በመከተል የማህበሩን መዋዕለ ነዋይ ስራ ላይ ማዋል፣

ሸ. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት፣

ቀ. የትርፍ አጠቃቀምን እና የትርፍ ክፍፍልን በተመለከተ ምክረ ሀሳቦችን ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፣

በ. የማህበሩ የሀብት እና የእዳ መግለጫ እንዲሁም የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ በማዘጋጀት ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ እንዲጸድቅ ማድረግ፣

ተ. የማህበሩን ፖሊሲዎች ማጽደቅ እና አፈጻጸማቸው ላይ ክትትል ማድረግ፣

ቸ. የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ከፍ/ቤቶች ውጪ መፍታት፣

ኀ. የማህበሩን የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ወይም/እና የሶስተኛ ወገን የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በዋስትና በማስያዝ ከማንኛውም ባንክ ወይም ባንኮች ወይም የገንዘብ ተቋማት ገንዘብ መበደር፣

ነ. የማህበሩ ተወካይ በመሆን አክሲዮኖችን በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት በመግዛት ስራውን እያከናወነ በሚገኝ እና/ወይም አዲስ በሚመሰረት የንግድ ማህበር ውስጥ ባለአክሲዮን እንዲሆን ውሳኔ ማሳለፍ። በተለይም ከማህበሩ ስራ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው ስራዎች በሚያከናውኑ ድርጅቶች ውስጥ፣

ኘ. የማህበሩን ዓላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ።

3) አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካሉት ስልጣኖች ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ በከፊል ስልጣኑን ለቦርዱ ሊቀመንበር ወይም ለማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 12
የዳይሬክተሮች ተጠያቂነት

1) በሕግ፣በመመስረቻ ጽሁፍ ወይም በመተዳደሪያ ደንብ እና በስብሰባዎች ላይ በሚተላለፉ ውሳኔዎች መሰረት ዳይሬክተሮች የተጣሉባቸውን ተግባሮች በጥንቃቄ የመወጣት ኃላፊነት አለባቸው፣

2) ኃላፊነቶቻቸውን ሳይወጡ በመቅረታቸው ምክንያት በማህበሩ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ዳይሬክተሮች በጋራ እና በተናጠል በማህበሩ ዘንድ ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፣

3) በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂነት የሚኖርባቸው ዳይሬክተሮች ከማህበሩ አጠቃላይ አስተዳደር ስራ ጋር በተያያዘ ስራቸውን በጥንቃቄ ማከናወን ይኖርባቸዋል።

4) የማህበሩን ሕልውና አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን ካወቁ እነዚህን ሁኔታዎች ለመከላከል ወይም ለመቀነስ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ሁሉንም አስፈላጊ እርምጃዎች ሳይወስዱ ቢቀሩ ዳይሬክተሮች በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል።

አንቀጽ 13
በዋስትና ስለሚያዙ አክሲዮኖች

1) እያንዳንዱ ዳይሬክተር በማህበሩ ውስጥ በስሙ ተመዝግበው ከሚገኙ አክሲዮኖች ውስጥ 10% (አስር በመቶ) በዋስትናነት ተቀማጭ ማድረግ አለበት፣

2) እነዚህ በዋስትና የተያዙ አክሲዮኖች ባለቤቶቻቸው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መሆናቸውን ካላቆሙ እና በማህበሩ ዘንድ የሚኖርባቸውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ እስካልተወጡ ድረስ ለባለቤቶቹ ተመላሽ አይደረጉም።

አንቀጽ 14
የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ

1) የማህበሩ የዕለት ተዕለት የአስተዳደር ስራዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሾም ዋና ስራ አስፈጻሚ የሚከናወን ይሆናል፣

2) ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ጨምሮ የዋና ስራ አስፈጻሚ የአገልግሎት ሁኔታዎች የሚወሰኑት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሆናል፣

3) የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ ስልጣንና ኃላፊነቶች በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 32 ስር በዝርዝር በተጠቀሰው መሰረት ይሆናል፣

4) የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ በውክልና የሚሰጡትን ሌሎች ስልጣኖች ተግባራዊ ያደርጋል።

አንቀጽ 15
ኦዲተሮች

1) መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ ኦዲተር ወይም ኦዲተሮችን ይሾማል። እንዲህ አይነቱ የኦዲተሮች ሹመት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መፅደቅ አለበት፣

2) የሚሾሙት ኦዲተሮች ህጋዊ ፣ ትክክለኛ ፈቃድ ያለው የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ሊሆን ይችላል፣

3) የኦዲተሮች ተግባር እና ኃላፊነት በንግድ ህግ ከአንቀጽ 368 እስከ 380፣ በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ይሆናል።

አንቀጽ 16
ማህበሩ የተመሰረተበት ጊዜ

ማህበሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተመስርቷል። ሆኖም በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 አንቀጽ 19 እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች መሰረት ሊፈርስ ይችላል።

አንቀጽ 17

የማህበሩ የሒሳብ ዓመት

የማህበሩ የሒሳብ አመት እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1 እስከ ጁን 30 ይሆናል።

አንቀጽ 18

ዘገባዎች

1) ማህበሩ በእያንዳንዱ የሂሳብ አመት ንብረቱን እና ዕዳዎች የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛን ዘገባ ያዘጋጃል፣

2) ማህበሩ ዘገባው በሚሸፍነው ጊዜ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች፣የታሰቡ እንቅስቃሴዎችን አጠቃሎ የሚያሳይ የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ ያዘጋጃል፣

3) ቦርዱ ዘገባዎቹን በመመልከት እና ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከሚደረግበት ቀን ቢያንስ አርባ አምስት (45) ቀናት ቀደም ብሎ ለባለ አክሲዮኖች ይልካል። እንዲህ አይነቱ ሰነድ እንደ አስፈላጊነቱ ለሌሎች ድርጅቶችም ይላካል።

አንቀጽ 19

ይፋ ማድረግ

ህትመቶች፣ ምዝገባዎች እና በህግ የሚፈለጉ ዘገባዎች ሁሉ በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና የንግድ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ይዘጋጃሉ።

አንቀጽ 20

ማሳወቂያ

1) የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ማሳወቂያ በመተዳደሪያ ደንቡ ከአንቀጽ 12 እስከ 14 በተጠቀሱ ሁኔታዎች መሰረት ይፈጸማል።

2) በማህበሩ ለባለአክሲዮኖች የሚሰጥ ማናቸውም ሌላ ማሳወቂያ በንግድ ህግ አንቀጽ 392 መሠረት ይፈጸማል።

አንቀጽ 21

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1) በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ በአማርኛው እና በእንግሊዘኛ ቋንቋው መካከል የትርጉም ልዩነት ቢኖር የአማርኛው ትርጉም ተፈጸሚነት ይኖረዋል።

2) ይህ የመመስረቻ ጽሁፍ ጠቅላላ ጉባኤው ከፈረመበት በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ ተረጋግጦ ከተመዘገበ እና ከጸደቀ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፣

ዛሬ በቀን _____ በ_____ ወር 200___ ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ ተዘጋጅቶ ተፈረመ።

የማህበሩ መስራች ባለአክሲዮኖች ስም፣ ፊርማ እና አድራሻ

ተ.ቁ	የባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም	ዜግነት	የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የተከፈለ የአክዮን ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	አድራሻ					ፊርማ	ቀን
						ከተማ	ክ/ከተማ	ቀበሌ (ወረዳ)	የቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር		
1	አቶ ክፍሌ ብርሃኑ ወንድሙ	ኢትዮጵያዊ	2,000	2,000		አ.አ	ቦሌ	03	23/1065	0911206600		፲፯/፲፩/09
2	አቶ ደጀኔ ወ/ማርያም በንቲ	ኢትዮጵያዊ	3,000	2,900	100	አ.አ	የካ	13	አዲስ	0911203019		17/11/09
3	ወ/ሮ አለምፀሐይ አለሙ ባቦ	ኢትዮጵያዊት	300	300		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	02	አዲስ	0911248157		
4	አቶ ፍቅሬ ዘውዴ ደጋጋ	ኢትዮጵያዊ	700	400	300	አ.አ	የካ	13	B553-18	0912506853		
5	አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ ታደሰ	ኢትዮጵያዊ	300	150	150	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	01	አዲስ	0911209085		
6	ወ/ሮ ወርቅነሽ መኮንን ጎንጥ	ኢትዮጵያት	300	300		አ.አ	የካ	02	MH39	0921778572		
7	ወ/ሮ ዶኔክ ተስፋዬ ዘሞ	ኢትዮጵያዊት	250	250		አ.አ	የካ	08	870	0911214654		
8	ወ/ሮ ሙሉ ጎበና ተሊላ	ኢትዮጵያዊት	100	100		አ.አ	ቦሌ	12	አዲስ	0921627774		
9	አቶ ማይክል መንገሻ ደለሉ	ኢትዮጵያዊ	200	100	100	አ.አ	አራዳ	01	395	0911516040		
10	አቶ አፈወርቅ ዮሐንስ ገርማሞ	ኢትዮጵያዊ	250	100	150	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	01	አዲስ	0911242303		17/11/09
11	ወ/ሮ ራሔል አካለወልድ ገ/ስላሴ	ኢትዮጵያዊ	300	200	100	አ.አ	አራዳ	11/12-03	1163	0911683737		
12	አቶ ወሰን አስፋው ቅጤሳ	ኢትዮጵያዊ	500	500		አ.አ	ኮ/ቀራንዮ	08	1904	0911206186		
13	አቶ ቴዎድሮስ አብርሃም ሀብተሚካኤል	ኢትዮጵያዊ	1,000	500	500	አ.አ	ቦሌ	02	062	0911200325		
14	አቶ ጋረደው አሰፋ ማሞ	ኢትዮጵያዊ	150	100	50	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	12	1208	0911665920		
15	አምባዬ አጋቶ አናታ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ቦሌ	6	155	0924849898		
16	የኔነሕ ሙሉጌታ ደነቀ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	12	አዲስ	0911542854		
17	አቶ ጌታቸው ማሞ አረዳ	ኢትዮጵያዊ	200	100	100	አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	1	አዲስ	0911642573		
18	አቶ ያዕቆብ ኢሣያስ ኪዳኔ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	አራዳ	7	498/ለ	0911903061		

ተ.ቁ	የባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም	ዜግነት	የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የተከፈለ የአክዮን ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	አድራሻ					ፊርማ	ቀን
						ከተማ	ክ/ከተማ	ቀበሌ (ወረዳ)	የቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር		
19	አቶ ገበየሁ አሸራ አየለ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	4	1507	0925273468		
20	አቶ ጌታሁን ካሣዬ መኩሪያ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ቂርቆስ	8	247	0913853776		
21	አቶ ምሰጋና መኩሪያ ዱራ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ን/ስ/ላፍቶ	4	433	0911424992		
22	አቶ አብዲ በቀለ ሀይሉ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ጉለሌ	07	962	0923992346 0911448996		
23	አቶ ይገረም ካሣ አባከሀ	ኢትዮጵያዊ	100	100		አ.አ	ቦሌ	11	B11/30	0911677459		
24	አቶ አስናቀ አማኑኤል አያሌ	ኢትዮጵያዊ	250	250		አ.አ	ቦሌ	03	19/271	0943044503		
25	ለማ ደገፉ ጉደታ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	300	200	100	አ.አ	ቦሌ	03	2032	0912625778		
26	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ	ኢትዮጵያዊ	1,000	1,000		አ.አ	ቦሌ	03	2185			
27	ወ/ሮ ትዝታ ከተማ ወዴሳ	ኢትዮጵያዊት	100	100		አ.አ	ቦሌ	01	አዲስ	0911632399		

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ ቅርንጫፍ (12)
ቁጥር ቅ(2) 181/ሃሀ/ሠ

በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል ።
አዲስ አበባ 25/11 ቀን 20 ሰዲ ዓ.ም

ሣራ ኃይሉ ጠ/ቂድቅ
SARA HAILU W/TSADIK
ከፍተኛ የሰነዶች ማረጋገጥ
ባለሙያ I
Senior Documents
Authentication Expert I

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ
ቅርንጫፍ (12)

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የተከፈለበት ምክንያት
የገንዘቡ ልክ ብር 477
በፊደል
ወይም ብር የሆነ ቴምብር
የደረሰኝ ቁጥር SB24AD
25 - 11 ቀን 20 09

የቴምብር ቀረጥ መክፈል አስፈፃሚ
ስም
ፊርማ